የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ የካቲት ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No. 12
ADDIS ABABA, 22nd February, 2022

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፮/፪ሺ፲፬ ዓ.ም

የፌደራል መንግሥት የተጨማሪ በጀት እና የወጪ አሸፋፈን ማስተካከያ አዋጅ............................ገጽ ፲፫ሺ፱፻፹

## Content

Proclamation No. 1266/2022

Federal Government Supplementary Budget and Financing Restructuring Proclamation……………page 13980

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፮/፪ሺ፲፬

## የፌደራል መንግሥት የተጨማሪ በጀት እና የወጪ አሸፋፈን ማስተካከያ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ ፶፭ (፩)፣ (፲፩) እና በኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰/፪ሺ፩ አንቀፅ ፳፯ መሰረት ለተጨማሪ መደበኛና ካፒታል ሥራዎች እንዲሁም ለ፪ሺ፲፬ በጀት ዓመት ከታክስ የሚገኘው ገቢ በመቀነሱ ከሀገር ውስጥ ብድር በመሸፈን የወጪ አሸፋፈንን ለማስተካከል የሚከተለው ታውጇል፡፡

**አንቀጽ ፩** ይህ አዋጅ "የ፪ሺ፲፬ በጀት ዓመት የፌደራል መንግሥት የተጨማሪ በጀት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፮/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1266/2022

## FEDERAL GOVERNMENT SUPPLEMENTARY BUDGET AND FINANCING RESTRUCTURING PROCLAMATION

In accordance with Article (55) (1) and (11) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and in accordance with Article 27 of the Federal Government of Ethiopia Financial Adminisration Proclamation No. 648/2009 a supplementary of Recurrent and Capital Budget and financing restructuring due to the reduction of tax revenue for deficit financing from domestic borrowing approved for the 2014 E.C budget year is hereby proclaimed.

**Article 1** This Proclamation may be cited as the "2014 Fiscal Year Supplementary Budget Proclamation No. 1266/2022."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**አንቀጽ ፪** ከሐምሌ ፩/፪ሺ፲፫ ጀምሮ እስከ ሰኔ ፴/፪ሺ፲፬ በሚፈጸመው በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከሀገር ውስጥ ብድር ከሚገኝ ገቢ ላይ ከዚህ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ውስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሎ እንደተመለከተው፡-

| | | |
|---|---|---|
| ሀ/ ለመደበኛ ወጪዎች | ብር | 106,000,000,000 |
| ለ/ ለካፒታል ወጪዎች | ብር | 7,000,000,000 |
| ሐ/ የወጪ አሸፋፈን ለማስተካከል | ብር | 9,000,000,000 |
| ድምር | ብር | 122,000,000,000 |

/አንድ መቶ ሃያ ሁለት ቢሊዮን ብር/ በተጨማሪ ወጪ ሆኖ በፌደራሉ መንግሥት እንዲከፈል በዚህ የተጨማሪ በጀት አዋጅ ተፈቅዷል፡፡

**Article 2** There is hereby appropriated a Supplementary Budget on the 2014 approved budget to the Federal Government, for the Fiscal Year commencing on Hamle 1,2013 E.C and ending on Sene 30,2014 E.C., from Domestic borrowing :-

| | | |
|---|---|---|
| (A)For Recurrent Expenditures | Birr | 106,000,000,000 |
| (B) For Capital Expenditures | Birr | 7,000,000,000 |
| (C) Financing Restructuring | Birr | 9,000,000,000 |
| Total | Birr | 122, 000,000,000 |

/One Hundred Twenty Two Billion Birr/ as set forth a schedule attached hereto.

**አንቀፅ ፫** ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ለየመሥሪያ ቤቶቻቸው ሥራና አገልግሎት ከሀገር ውስጥ ብድር ከሚገኝ ገቢ በዚህ አዋጅ ለተጨማሪ ሥራዎች የተፈቀደላቸውን ተጨማሪ በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ የገንዘብ ሚኒስትሩ እንዲከፍል ተፈቅዶለት ታዟል፡፡

**Article 3** The Minister of Finance is hereby authorized and directed upon the request of the heads of the concerned government organs, to disburse out of the domestic borrowing the additional amount appropriated herein for the undertakings of their respective organs.

**አንቀጽ ፬** በዚህ አዋጅ የተፈቀደው የተጨማሪ በጀት በ፪ሺ፲፬ በጀት ዓመት የበጀት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፶፬/፪ሺ፲፫ በተመለከተው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**Article 4** Utilization of the Supplementary Budget shall be made in accordance with the 2014 E.C. budget year Budget Proclamation No. 1254 /2021.

**አዲስ አበባ የካቲት ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**Done at Addis Ababa, on this 22nd Day of February, 2022.**

**SAHLE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**